# ጥናት አንድ ሚክያስ 1፡1-2፡13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ወርዶ በምድር ከፍታዎች ላይ እንደሚራመድ፣ ተራሮች ከሥሩ እንደሚቀልጡ፣ ሸለቆዎች እንደሚሰነጠቁ፣ በእሳት ፊት እንዳለ ሰም፤ በገደል ላይ እንደሚወርድም ፈሳሽ እንደሚሆኑ ነው ነብዩ ሚክያስ የሚናገረው። ለሰዎች ሁሉ አስደናቂና አስገራሚ እንዲያውም አስፈሪ በሆነ መንገድ ሲገለጥ የፈለገበትን ምክንያት ሲነግረን፤ ቁ5 ላይ "ይህ ሁሉ የሚሆነው ስለ ያዕቆብ በደል፤ ስለ እስራኤልም ቤት ሐጥያት ነው።" በማለት ግልጽ አድርጎ አንዳችም መሸፋፈን በሌለበት መልኩ ይነግረናል።
2. በአዲስ ኪዳን ውስጥ በ1ኛ ጴጥ 4፡17 ላይ የሰፈረው የእግዚአብሄር መመሪያ በዚህም ላይ ይሰራል፤ ማለትም እግዚአብሄር በሌሎች ላይ የማይፈርድ ሆኖ ሳይሆን፤ ነገር ግን በቅድሚያ መሆን እንዳለበት የሚነግረን ፍርድ የሚጀምረው ከእግዚአብሄር ቤት እንጂ በውጭ ባሉት ላይ እንዳልሆነ ግልጽ ሆኖ ሰፍሮልናል። እግዚአብሄር አምላክ ይህንን ዓይነቱም መመሪያ መጠቀም የወሰነበት ምክንያት እኔ እንደሚመስለኝ፤ የእግዚአብሄር ሕዝቦች ሕይወታቸውን ከእግዚአብሄር ጋራ ካስተካከሉና በቅድስና መኖር ከጀመሩ በአካባቢያቸው ባሉት አህዛብ ላይ ለውጥ ለማምጣት ብርሃንና ጨው በመሆን በመሆን ጎረቤቶቻቸው ከፍርድ እንዲድኑ ማድረግ ይችሉ ይሆናል።
3. በትንቢተ ዮናስ መጽሐፍ ውስጥ ነብዩ በዮና 3፡4 ላይ ትንቢቱን ሲናገር እነዚህ ሰዎች እውነት ሰምተው ልባቸውን ወደ እግዚአብሄር እንዲመልሱ ሳይሆን፤ ይህንን ዓይነት መልዕክት እንዲያስተላልፍ ግድ ስለተባለ ብቻ ሲሆን፤ በዚህ ቦታ ግን ሚክያስን ስንመለከተው ለሕዝቡ ያመጣው መልዕክት እርሱንም ጭምር እንዳስለቀሰው፣ ዋይ እንዳሰኘውና ባዶ እግሩን፣ እርቃኑንም ጭምር እንዲሄድ እንዳደረገው እናያለን። የእግዚአብሄርን ቃል በተለይም ደግሞ የፍርድን መልዕክት ለሰዎች ለመንገር ይዘን ስንመጣ በግድ የለሽነት መንፈስ ሳይሆን ልባችን ለእነርሱ የምናፈስና ርህራሄን በተሞላ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ እንማራለን።
4. ገና ምዕራፍ ሁለትን ሲጀምር ነብዩ ያተኮረባቸው ሰዎች ማንነታቸውን ሲገለጽ፤ ክፉ ለመሥራት የሚያቅዱ፣ በመኝታቸው ሳሉ ተንኮል የሚያውጠነጥኑ በማለት ይገልጻቸዋል። በእግዚአብሄር ዓይን ማናቸውም ዓይነት ሃጥያት ተቀባይነት እንደሌለውና ሃጥያት ሁሉ ፍርድን እንደሚያስከትል ብናውቅም እንኳን፤ የእነዚህን ሰዎች ሃጥያት ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር ተሳስተው፣ ወይም ሳያስቡት በድንገት የሚያደርጉት ሳይሆን አቅደው፣ ፕላን አድርገው፣ አውጠንጥነው፣ አስበውና አሰላስለው የሚፈጽሙት መሆኑ ሃጥያታቸውን የጎላ ያደርገዋል።
5. የእነዚህ ሰዎች የልብ ሁኔታ የሚናገረው ቃል "ይመኛሉ" የሚለው ወይም "ምኞት"እንደሆነ እናያለን። እውነትም የሰው ልጅ ማድረግ የሚፈልገውን ሁሉ ማድረግ የሚችልበት ሃይልና አቅም ቢኖረው ወይም ሁኔታዎች ሁሉ ሊያደርግ ለሚፈልገው ነገር የተመቻቹ ሆነው ቢያገኛቸው፤ እግዚአብሄርን በመፍራት ብቻ ሃጥያትን ከማድረግ የሚመለስ ሰው ቁጥር ምን ያህል እንደሚሆን አላውቅም፤ ሆኖም በዚህ ክፍል ስለምናያቸው ሰዎች ሲናገር "ሲነጋ በማለዳ ይፈጽሙታል፤ የሚያደርጉበት ሃይል በእጃቸው ነውና።" ስለሚል፤ እነዚህ ሰዎች በአልጋቸው ላይ ያሰቡትን በሥራ ለመተርጎም ምክንያት ከሆናቸው ነገር ዋነኛው ሃይሉ በእጃቸው መሆኑ ወይም ለማድረግ ሥልጣኑ ስላላቸው ነው።
6. እነዚህ ሰዎች ይፈጽሟቸው ከነበሩት ብዙ ሃጥያቶች ጋራ ወይም ደግሞ ይፈጽሙ የነበሩትን ሃጥያቶች ይፈጽሙ የነበሩበትን ውስጣዊ ነገር እግዚአብሄር ሲያጋልጥ በተለይ በቁ3 ላይ በትዕቢት በተሞላ መንፈስ ያደርጉት እንደነበረ ነው ነብዩ ግልጽ የሚያደርግልን። በመዝ 105፡44 ላይ እግዚአብሄር አምላክ የአህዛብ የሆነውን መሬትና እነርሱ የለፉበትን ነገር ሁሉ ላለፉበት ለእስራኤላውያን እንደሰጠ ሲነግረን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ግን በተለይም በቁ4 ላይ እንደምንመለከተው ለማረኳቸው ለአህዛብ ሳይለፉ እንዲጠቀሙበት እርሻዎቻቸውንና ምድራቸውን እንደሰጠ ስናይ የተገላበጠ ነገር እያደረገ እንደሆነ እናያለን።
7. እነዚህ የሐሰት ነብያት የእግዚአብሄርን ትክክለኛ መልዕክት ማምጣትና ሕዝቡን ከክፉ መንገዱ ለመመለስ ከመሞከር ይልቅ ሕዝቡን ወደ በለጠ ሃጥያትና ክፋት ለመምራት የእግዚአብሄር እውነተኛ መልዕክት ለህዝቡ የሚያመጣውን ሰው እንዳይናገር በመከልከል ራሳቸውንና ህዝቡን እንደሚያስቱ በቁ6 ላይ እናነባለን። የእስራኤል ህዝብና ሃሰተኛ ነብያቶቻቸው እውነተኛ የእግዚአብሄር መልዕክቶኞችን ለመናገር ይከልክሉ እንጂ በቁ11 ላይ እንደምናነበው እንደ እነርሱ በሐሰተኛ መልዕክት ተሞልተው የሚናገሩትን እንዲጨምሩና እንዲናገሩ እንደሚያበረታቷቸው እናያለን።

## ጥናት ሁለት ሚክያስ 3፡1-12 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አንድን አገር ለመምራትና ለማስተዳደር በሕዝብ ላይ የተሾሙ ሰዎች በሰው ዘንድ ብቻ ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሄር ዘንድ የሚጠበቅባቸው ሌሎች ብዙ ነገሮች ቢኖሩም እንኳን፤ በዚህ ቦታ ግን እግዚአብሄር በባርያው በኩል መሰረታዊ የሆነውን ከመሪ የሚጠበቀውን ነገር ይናገራል፤ ይኸውም ፍትህን ማወቅ የሚለው ሃሳብ ነው። እነዚህ ሰዎች ፍትህን እንደማያውቁና እንደማይከተሉ በማረጋገጫነት በቁ2 ላይ የተጠቀሱት ሁለት ሃሳቦች፤ የመጀመሪያው መልካሙን የሚጠሉ ሰዎች መሆናቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የሚወዱ ሰዎች መሆናቸው ነው።
2. እነዚህ በቁ1-3 ውስጥ የተመለከትናቸው የያዕቆብ መሪዎችና የእስራኤል ገዦች ከማንነታቸው አልፎ እግዚአብሄር ስለ ድርጊታቸውም ጭምር የተናገረ ሲሆን፤ በቁ4 ላይ ግን የምናየው እውነተኛ የእግዚአብሄር አገልጋይና የህዝብ እረኛ ማድረግ ያለበትን ነገር ሲያደርጉ ነው የምናየው፤ ይኸውም ወደ እግዚአብሄር መጸለያቸው ነው። ለዚህ ለሃይማኖታዊ ድርጊታቸው የእግዚአብሄር ምላሽ ጩኸታቸውን አለመስማትና ፊቱንም ከእነርሱ መሰወር ሲሆን፤ ለዚህም ምክንያት አድርጎ ያስቀመጠልን ካደረጉት ክፋት የተነሳ እንደሆነ ቁ4 ግልጽ አድርጎ ይናገራል።
3. በቁ5 ላይ እግዚአብሄር ለእነዚህ ሰዎች የሰጣቸው ስም “ሕዝቤን የሚያስቱ ነብያት” የሚል ነው። እነዚህ ሃሰተኖች እንደሆኑና የእግዚአብሄርን ሕዝብ እንደሚያስቱ የተነገረላቸው ነብያት ለሚያበሏቸውና ለማያበሏቸው ሰዎች ሁለት የተለያየ ዓይነት ነገር እንደሚያደርጉ እናነባለን፤ ለሚያበሏቸውና የሚፈልጉትን ነገር ለሚሰጧቸው ሰዎች የሰላምና የበረከት ትንቢት እንደሚያመጡ፤ ለማያበሏቸውና የሚፈልጉትን ነገር ለማያደርጉላቸው ደግሞ የማስፈራራትና የጦርነት ዓዋጅን እንደሚያውጁበት እናያለን። ልክ በሚክያስ ዘመን እውነተኞችም ሃሰተኞችም ነብያት እንደነበሩ ሁሉ በእኛም ዘመን ሲኖሩ፤ ላበላቸውና ወደፊት ደግሞ ሊያበላቸው እንደሚችል ለሚገምቱት ሰው ሰላምንና በረከትን መተንበያቸው፤ ለማያበላቸውና በሚቃወማቸው ላይ ደግሞ ጦርነትን እንደሚያውጁበት በየጊዜው የሚሰማ ነገር ነው።
4. ሌሊቱ ያለ ራዕይ እንደሚመጣባቸው፣ ጨለማውም ያለ ንግርት እንደሚመጣባቸው፣ በነብያቱ ላይ ጸሐይ እንደምትጠልቅባቸውና ቀኑም እንደሚጨልምባቸው፣ ባለራዕይ ነን ባዮቹ እንደሚያፍሩ፣ ንግርተኞች እንደሚዋረዱ፣ እግዚአብሄር መልስን ስለማይሰጣቸውና ከእርሱ የሆነ ምንም ዓይነት መልዕክትን ስለማይቀበሉ ሁሉም በእፍረት ፊታቸውን እንደሚሸፍኑ ይናገራል። እነዚያ ላበላቸው ሰላምን፤ ላላበላቸው ደግሞ ጦርን የሚናገሩ ሲሆን፤ ሚክያስ ደግሞ ለሁሉም እግዚአብሄር ያለውን ብቻ የሚናገር ነው፤ እነዚያ ከእግዚአብሄር ጋራ ግንኙነት የሌላቸው ሲሆኑ፤ ሚክያስ ግን የሚናገረውን የሚቀበለው ከእግዚአብሄር መንፈስ ነው፤ እነዚያ ፍትህን የማያውቁ ሲሆኑ፤ ሚክያስ ግን ፍትህንና ብርታትን የተሞላ ነብይ ነው።
5. ነብዩ ሚክያስ ምንም እንኳን ከላይ ባየናቸው ቁጥሮች ውስጥ ስለ ያዕቆብ ቤት መሪዎችና ስለ እስራኤል ቤት ገዦች የተናገረ ቢሆንም፤ በዚህ ቁጥር ላይ ደግሞ ነብያቱን ለጊዜው ተወት በማድረግ ለመሪዎቹና ለገዦቹ ሲናገር የሚከተሉትን ሶስት ነገሮች ነው የሚናገረው፤ በአንደኛ ደረጃ እነዚህ ሰዎች ለፍትህ ምንም ቦታ የማይሰጡና ፍትህን የሚንቁ ሰዎች እንደሆኑ ነው፤ ሁለተኛው የተጣመመውን ነገር ይቅርና፤ ትክክለኛ የሆነውን ነገር እንኳን የሚያጣምሙ ሰዎች ናቸው፤ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ከተሞቻቸውን የሚገነቡት በክፋትና ደምን በማፍሰስ እንደሆነ ያስገነዝበናል።
6. እነዚህ በተለያየ መንገድ የእግዚአብሄርን ሕዝብ እንዲመሩ የተቀመጡት ሰዎች፤ የሕዝብ አስተዳዳሪ መሪዎች፣ የሕዝብ አስተማሪ ካሕናትና፣ ከእግዚአብሄር ቃልን ሊያመጡ የተቀመጡት ነብያት ጭምር አገልግሎታቸውን ለማገልገል ከህዝቡ የሚጠብቁት ነገር እንዳለ በተለያየ መንገድ የተናገረው ሲሆን፤ በአንድ ቃል ለመግለጽ ግን ሁሉም “ገንዘብ” ወይም “ክፍያ” ይጠይቃሉ። ነብዩ ምክያስ ለምን እግዚአብሄር ምድሪቱን ሊያፈርስና ለፍርድ እንድትዳረግ ያደረጋትን ምክንያት በቁ12 ላይ ሲገልጽ “በእናንተ ምክንያት” በማለት በመሪዎቿ፣ በካሕናቶቿና በነብያቷ ምክንያት ይህ ፍርድ ሊመጣባት እንደቻለ ይነግረናል።
7. የሰውን ስጋ የሚበላ፣ የሰዎችን ዓጥንት በመሰባበርና በመብላት እና በአጠቃላይ በቁ2-3 ውስጥ እነዚህ የያዕቆብ መሪዎችና የእስራኤል ገዦች ያደርጉታል በማለት እግዚአብሄር የሚከስበትን ክስ ስናይ፤ በተፈጥሮው የዚህ ዓይነት ነገሮችን ያደርጋል ተብሎ የሚታወቀው የዱር አውሬ ብቻ እንደሆነ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው። እግዚአብሄር እነዚህ ሰዎች እውነትም እንደ አውሬ ቃል በቃል የሰው ስጋ ይበላሉ ለማለት ሳይሆን፤ እነዚህ የሕዝብ መሪዎች የሚያምኑት የሕዝቡ መኖር ለእነርሱ ኑሮ ማበልጸጊያና የሚፈልጉትን ለማግኘት የሚጠቀሙበት መሳሪያ እንጂ ሕዝቡን ለማገልገል ከእግዚአብሄር የተቀበሉት ሃላፊነት እንደሆነ ያልገባቸው ሰዎች መሆናቸውን ለመናገር ነው።

# ጥናት ሶስት ሚክያስ 4፡1-5፡15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዛሬ በሰዎች ዘንድ በከፍታቸውና በትልቅነታቸው ታዋቂ የሆኑ እንደ ኤቨረስትና የመሳሰሉ ትላልቅ ተራሮች እንዳሉ፤ ተራራ የመውጣት ስፖርት የሚያዘወትሩ ሰዎችም ወደ እነዚህ ትላልቅ ከፍታዎች እንጂ ወደ ጽዮን ተራራ እንደማይሄዱ ይታወቃል። ሚክያስ ግን የጽዮን ተራራ በሁሉም ዘንድ ከፍ ብሎ የሚታይበት ቀን እንደሚመጣና ያንንም ቀን "የመጨረሻው ዘመን" በማለት ይጠራዋል። የጽዮን ተራራ በአንድ ጊዜ ቁመቱ ጨምሮ ከትላልቅ ተራሮች የሚበልጥበት ጊዜ ይመጣል ማለት ሳይሆን፤ በመጨረሻው ዘመን የነገሮች ሁሉ ትኩረት በኢየሩሳሌም ዙሪያ በሚሆንበት ጊዜ፤ የጽዮን ተራራ በዝና፣ በታዋቂነትና፣ በክብር ከፍ ካሉት ሁሉ በላይ ከፍ እንደሚል ለመናገር ነው።
2. ሰዎች ቃሉን ከእርሱ ለመማር ወደ እግዚአብሄር ተራራ ይመጣሉ፣ እርሱ በሕዝብ መሃል ፈራጅ ይሆናል፣ በመንግሥታት መሃል ያለውን ግጭት ያቆማል፣ ሰው ሁሉ በገዛ ወይኑና በለሱ ሥር ይቀመጣል ማለትም አንዱ ከሌላው የሚፈልገው ነገር አይኖርም፣ የሚያስፈራቸው ነገር አይኖርም፣ ሰው ሁሉ የፈለገውን የማምለክ መብት ይኖረዋል። ለእኔ እንደሚገባኝ ከሆነ፤ ሚክያስ ስለ ማጭድና  ሰይፍ መቀጥቀጥና መቀየር ለመናገር ሳይሆን፤ ሰዎችን ለማጥፋት ተብለው የተሰሩት መሳሪያዎች ለልማት በሆነ ነገር ላይ ይውላሉ ማለት ነው፤ ለምሳሌ የኑክሊየርን ሃይል ለጦርነት ሳይሆን ለሃይል ማመንጫነት እንደመጠቀም ማለት ይመስለኛል።
3. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም በብዙዎቹ የነብያት መጽሐፍት ውስጥ የምናየው የአጭሩንና የረጅሙን ዘመን ትንቢት በማደባለቅ እንደሚናገሩ ይታወቃል። በ4፡10 ላይ እግዚአብሄር ሕዝቡ ወደ ባቢሎን እንደሚሄድና ከዚያም እንደሚታደጋቸው የአጭሩን ጊዜ ትንቢት ሲናገር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቁ7ትን ስናነብ እግዚአብሄር አምላክ በጽዮን ተራራ በእነርሱ ላይ የሚነግስበትን የሺህ ዓመቱን አገዛዝ ይናገራል። እነርሱ ራሳቸውን እንዳሰባሰቡ መስሎ ይታያቸው እንጂ ቁ12-13 የሚነግረን በጽዮን ልጅ ተረግጠው ይደቅቁ ዘንድ እግዚአብሄር ራሱ በአውድማ ላይ እንዳለ ነዶ ለመሰብሰብ ባለው እቅድና ፕላን መሰረት የሚካሄድ ነገር እንደሆነ በግልጽ አስቀምጦታል።
4. በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ጉንጩን በበትር እንደሚመታ የተነገረለትን የእስራኤል ገዢ በቁ1 ላይ ስንመለከት፤ በሁለተኛ ደረጃ የምንመለከተው ደግሞ በቁ2 ላይ ከብዙ ጊዜ በኋላ ለእስራኤል የሚመጣላት ገዢ ሆኖ የተነገረውን እናያለን። ስለ አንደኛው ገዢ ብዙ የተነገረ ነገር ባናይም እንኳን በቁ2 ላይ ስለተነገረው ገዢ በሌሎች ቁጥሮች ውስጥ የተነገረውን ሳንጨምር በዚህ ቁጥር ላይ ብቻ የምንመለከታቸው ነገሮች፤ አመጣጡ ከቤተልሄም ኤፍራታ እንደሚሆን፣ አመጣጡ ከጥንት እና ከቀድሞ ዘመን እንደሆነና የእስራኤል ገዢ እንደሆነ ማየት እንችላለን።
5. በሌሎች ቁጥሮች ውስጥ ስለዚህ ሰው ከተመለከትናቸው ሃሳቦች በተጨማሪ የማያቸው ነገሮች፤ አንደኛው በእግዚአብሄር ሃይልና በአምላኩ በእግዚአብሄር ስም ታላቅነት ጸንቶ የሚቆም መሆኑ፤ መንጋውን የሚጠብቅ መሆኑ፤ በዚያን ጊዜ ሃያልነቱ እስከምድር ዳርቻ ስለሚደርስ ሕዝቡ ተደላድለው እንዲቀመጡ ያደርጋቸዋል፤ እርሱ ሰላማቸው ይሆናል። እነዚህንና ሌሎቹንም ስለዚህ ገዢ ስንመለከት ይህ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ለማየት አያስቸግረንም፤ ምክንያቱም በማቴ 2፡5-6 ላይ ስናነብ በሚክያስ ውስጥ ስለዚህ ገዥ የተነገረው ነገር ለኢየሱስ እንደሆነ ከአዲስ ኪዳን መረዳት የምንችል ሲሆን፤ በተጨማሪም "እርሱ ሰላማቸው ይሆናል" የሚለው አነጋገር በቀጥታ ወደ ኢየሱስ የሚያመለክት ነው።
6. ይህንን በአሶራውያን የመወረርና የድንበር መደፈር በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በተናገረበት አፉ፤ በቁ6 መጨረሻ ላይ ስናነብ "እርሱ ነጻ ያወጣናል" በማለት ከላይ ባየናቸው ቁጥሮች ውስጥ ኢየሱስ ብለን ያልነው ሰው ነጻ ለመውጣታቸው ምክንያት እንደሚሆን ነው የሚነግረን። በዚያን ጊዜ እግዚአብሄር በሕዝቡ መሃል ሊያደርግ የተዘጋጀው ነገር፤ ፈረሶቻቸውን ማጥፋት፣ ሰረገሎቻቸውን መደምሰስ፣ ከተሞቻቸውን መደምሰስ፣ ምሽጎቻቸውን ማፈራረስ፤ ማለትም እነዚህ ሁሉ የሚያመለክቱን የሚታመኑባቸውን ነገሮች ሁሉ ከእነርሱ መውሰድ ሲሆን፤ ሌሎች ደግሞ ልባቸውን ከእግዚአብሄር የሚመልሱትን ነገሮችም ሁሉ ከእነርሱ እንደሚያስወግድ ነው የሚናገረው።
7. ሚክያስ የሶስተኛውን ምዕራፍ ሲጨርስ በእግዚአብሄር ተራራ ላይ የሚደርሰውን አስከፊና አሳዛኝ ሁኔታ ሥዕላዊ በሆነ መልክ በቁ12 ላይ የሚገልጽ ሲሆን፤ ምዕራፍ አራትን ሲጀምር ደግሞ ይኸንነው የእግዚአብሄር ተራራ በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሄር ሊያደርሰው ያሰበበትን ከፍታ እናነባለን። እነዚህን ሁለት አጠገብ ለአጠገብ የሰፈሩትን ቁጥሮች በማነጻጸር ስንመለከታቸው፤ አምላካችን አንድ ቀን ሊነሳ ይችላል ተብሎ ያልተገመተውን ነገር በወደደው ጊዜና በፈቀደው ሰዓት ወደ ተለየ ክብር ሊያመጣ እንደሚችል እንማራለን።

# ጥናት አራት ሚክያስ 6፡1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ1 እና በቁ2 ላይ በእግዚአብሄርና በሕዝቡ መካከል ያለውን ክርክር እንዲሰሙ በእግዚአብሄር ሲጋበዙ የምንመለከታቸው፤ በመጀመሪያ ደረጃ የተጠሩት ተራሮች ሲሆኑ፣ ቀጥሎ ደግሞ ኮረብቶችን፣ ከዚያም በመቀጠል የምድር ጽኑ መሰረቶችንም በምስክርነት መልክ ሲጠራቸው ይታያል። የፍጥረት ሁሉ ዳኛና ቅን ፈራጅ የሆነው እግዚአብሄር በፍጥረቱ ፊት ለክርክር ራሱን እንዳቀረበ የምናይ ሲሆን፤ ሕዝቡ እንዲመልሱለት የሚጠይቃቸው ሁለት ጥያቄዎች፡ አንደኛው "ሕዝቤ ሆይ ምን አድርጌሃለሁ?" የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ "ሸክም የሆንኩብህስ እንዴት ነው?" የሚል ነው።
2. ለክርክሩ እንደ መግቢያ በመጠቀም ሁለት ጥያቄዎችን ከጠየቃቸው በኋላ ከእነርሱ ምላሽን ሳይጠብቅ ወዲያው በማከታተል ለእነርሱ ያደረጋቸውን ሶስት ነገሮች መናገር ይቀጥላል፤ እነዚህም ከግብጽ ምድር ማውጣቱ፣ ከባርነት ምድር መቤዠቱና፣ በመጨረሻም ሕዝቡን በመምራት እንዲያገለግሏቸው ሙሴን፣ አሮንንና፣ ማርያምን እንደሰጣቸው ይነግራቸዋል። ከዚህ ነገር እኔ የምማረው ነገር ቢኖር፤ በእውነት ከእግዚአብሄር የሚሰጡን መሪዎች በእርሱ ዓይን ትልቅ ሥፍራ እንዳላቸውና እኛም ደግሞ በዚያ መልኩ ልንቀበላቸው እንደሚገባን እማራለሁ።
3. እግዚአብሄር በሕዝቡ ሕይወት ካደረጋቸው ብዙ ነገሮች መሃል ወደ ኋላ ተመልሰው እንዲያስታውሱ የሚነግራቸው ሁለት ነገሮች፤ የመጀመሪያው ባላቅ የመከረውን ምክርና በለዓም ደግሞ ለዚያ የመለሰለትን ምላሽ እንዲያስታውሱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከሰጢም እስከ ጌልጌላ ያደረጉትን ጉዞ የተመለከተ ነው። እግዚአብሄር እነዚህን ነገሮች ሕዝቡ እንዲያስታውሱ የማድረጉን ምክንያት በዚሁ ቁጥር ላይ የምናገኝ ሲሆን ይኸውም "የእግዚአብሄርን የጽድቅ ሥራ ታውቁ ዘንድ" ነው በማለት ይነግራቸዋል።
4. እስራኤል እግዚአብሄርን እንደበደለ ሃጥያተኛነቱን መቀበሉን በቁ6-7 ላይ የተነገሩት ሃሳቦች ሁሉ የሚጠቁሙን ሲሆን፤ ከሁሉ በላይ ግን ግልጽ በሆነ መንገድ የሚናገረው በቁ7 ላይ የሰፈረው "ስለ በደሌ የበኩር ልጄን…ላቅርብለትን" በማለት የሰፈረው ሃሳብ እንደሆነ ነው የምመለከተው። አዎን በዚህ ክፍል ውስጥ እስራኤል ሃጥያተኛነቱን እንደተቀበለ ሆኖ ቢሰፍርልንም እንኳን፤ ለሃጥያቱ ግን መፍትሄ ሊሆኑ ይችሉ እንደሆነ በማለት የሚሰነዝራቸው ነገሮች ግራ መጋባቱን ይጠቁሙናል፤ ሆኖም በሶስቱም ውስጥ ግን ማዕከላዊ ሆኖ የማየው ሃሳብ፤ ለሃጥያቱ ሥርየት መሥዋዕት መሆን ያለበት ነገር እንዳለ መረዳቱን ከሶስቱም ጥያቄዎቹ ማየት እንችላለን።
5. እግዚአብሄር አምላክ ፈቃዱን ለሰው ልጆች በተለይም ለእስራኤል ሲያስታውቅ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳልነበረ የሚጠቁመን ሃሳብ፤ በዚሁ ቁ8 ላይ የተነገረው "ሰው ሆይ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል" የሚለው አነጋገር ነው። ሕዝቡ እዚህ ሥፍራ ላይ ግራ በመጋባት የጠየቋቸው ጥያቄዎች መቅረብ የነበረባቸው በጊዜው በክህነት አገልግሎት ላይ ለነበሩት ሰዎች እንደነበረ የሚታወቅ ነው፤ ሆኖም በዚህን ወቅት ካህናቱ ሁሉ በሚክ 3፡11 ላይ እንደምናየው የሚሰሩት በክፍያ ስለሆነ የሕዝቡን ጥያቄ ማስተናገር አይፈልጉም ማለት ነው።
6. በቁ8 ላይ የሰፈሩት እግዚአብሄር ከእነርሱ የሚጠብቃቸው ነገሮች ሶስት እንደሆኑ የምናይ ሲሆን እነዚህም፡ የመጀመሪያው ፍትሕን ማድረግ፤ ሁለተኛው ምሕረት ማድረግን እንዲወዱና፤ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ በአምላካቸው ፊት በትህትና ይራመዱ ዘንድ መሆኑን እናያለን። በቁ7 ላይ የተጠየቁት ጥያቄዎች፤ አንደኛው የአንድ ዓመት ጥጃ ማቅረብ፣ ሁለተኛው ደግሞ አንድ ሺህ አውራ በጎች እና አስር ሺህ የዘይት ፈሳሽ፣ በመጨረሻ ደግሞ የበኩር ልጃቸውን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ ሲሆን፤ እግዚአብሄር የሰጣቸው መልስ እነርሱ ካሰቧቸው አማራጮች በብዙ እጥፍ የተሻሉና ቀላል እንደሆኑ ነው ለእኔ የሚታየኝ።
7. በሃጥያታቸው ምክንያት ከእግዚአብሄር ዘንድ የሚመጣባቸው ነገር የሚከተለው ነው። ይበላሉ ሆኖም ግን አይጠግቡም፣ ያከማቻሉ ነገር ግን አይጠራቀምላቸውም፣ የሚሰበስቡትን ነገር ደግሞ ለሰይፍ ያደርገዋል፣ ይዘራሉ ነገር ግን አያጭዱም፣ የወይራ ዘይት ይጨምቃሉ፤ ሆኖም ከዘይቱ አይቀቡም፣ ወይን ይቆርጣሉ፤ ከወይን ጠጁ ግን አይጠጡም።
8. በዚያን ዘመን በእስራኤል ላይ የነገሱት ነገሥታት ሁሉም ለማለት ይቻላል በእግዚአብሄር ፊት ክፉ ያደረጉ እንደነበረ ታሪካቸውን ስናነብ ማየት እንችላለህ፤ ሆኖም እነዚህ እግዚአብሄር ከሌሎቹ ለይቶ የሚናገርላቸው አባትና ልጅ በ1ኛ ነገ 25-33 ላይ ስናነብ እጅግ ክፋትን በእስራኤል ላይ ከማምጣት አልፈው በበዓል ጣዖት ቤተ መቅደስ ውስጥ እንኳን ሳይቀር መሰዊያን ለመስራት የደፈሩ ሰዎች በመሆናቸው የእግዚአብሄርን ቁጣ እንዲነድ ያደረጉ ነገስታት እንደሆኑ፤ እንዲያውም ያ ክፍል ሲነግረን ከእነርሱ በፊት ከነበሩት ክፉ ነገሥታት በላይ ክፋትን እንዳደረጉ ስለ እነርሱ የሰፈረው ታሪክ ይናገራል።

# ጥናት አምስት ሚክያስ 7፡1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ነብዩ ራሱንም ከህዝቡ ጋራ ደምሮ በተከሰተው ሁኔታ በሃዘን ውስጥ እንዳለ ሲናገር፤ በተለይም ቁ2 ላይ ከምንመለከተው ሃሳብ ተነስተን ለሁኔታው ምክንያት ነው ብለን ማለት የሚያስችለን የመጀመሪያው ነገር፤ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለበት ሰው መጥፋቱ፤ ቅን የሆነ ሰው አለመኖሩ፤ ሰው ሁሉ ደግሞ ደም ለማፍሰስ ማድባቱና፤ አንዱ ሌላውን ለማጥመድ መረብ መዘርጋት ተግባራቸው ስላደረጉት ነው። ቁ3 ላይ ስንመለከት ገዥ ሆነው በሕዝብ ላይ የተቀመጡት እጅ መንሻ እንደሚፈልጉ፤ ፈራጅ ተብለው ለሕዝብ እንዲፈርዱ የተቀመጡት ደግሞ ጉቦን እንደሚቀበሉ ማየት እንችላለን።
2. እንደ እነዚህ ያሉ በክፋት የተሞሉና ከራሳቸው በስተቀር ለሕዝብ የማይራሩ ጨካኝ ባለሥልጣኖች ሁሉ አንድ ሲሆኑና ሲስማሙ ሕዝቡ አቤት ሊል የሚችልበት ምንም ዓይነት ሁኔታና መንገድ እንዳይኖር አንዱን በሌላው ከሶ ፍትህ እንዲገኝ ለማድረግ በሩን እጅግ የጠበበ እንዲሆን ያደርገዋል። ቁ4 ላይ የተሻሉና በጣም ቀና ሰዎች ናቸው የተባሉት እንኳን እንደ አሜከላና እንደኩርንችት የሚቆጠሩ ከሆነ፤ ሌሎቹ ክፉዎችና ተንኮለኞች የሚባሉት ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት አዳጋች አይሆንም።
3. ሃጥያታቸው ብዙ ዓይነት መዘዞችን ያስከተለ እንደሆነ ቢታወቅም እንኳን በቁ5ት ላይ የምንመለከተው ደግሞ በጣም ሕብረተሰቡ በትክክለኛ መንገድ አብሮ ለመኖር የሚያስችለውን ነገር እንዳስጣለው ነው የምንመለከተው፤ ይኸውም “አለመተማመን” የሚለው ሲሆን ባልንጀራ እንዳይተማመን ሆኗል፤ በትዳር ጓደኞች መሃል መተማመን ርቋል፤ በወላጅና በልጅ፤ በምራትና በአማት…መተማመንን አጥፍቷል።
4. በአዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ “አንተ ግን” በማለት ጳውሎስ የተናገረው ሰው ጢሞቲዎስ ይባላል። ይህ ሰው በአካባቢው ያለው ሰው ሁሉ ለራሱ ብቻ የሚሮጥ፣ ስለሌላው ደንታ የሌለውና፣ የሚያስፈልገውን ለማግኘት ደም ከማፍሰስም እንኳን እንደማይመለስ ተመልክቶ በራሱ “እኔ ግን እግዚአብሄርን ተስፋ አደርጋለሁ፤ አዳኜ የሆነውን አምላክ እጠብቃለሁ” ለማለት እንደቻለ ሁሉ፤ እንባቆምም በሶስተኛው በቁ17 ላይ ብዙ የማይመቹና ክፉ በሚመስሉ ነገሮች ውስጥ ቢገኝ እንኳን “እኔ ግን በእግዚአብሄር ደስ ይለኛል፤ በድነቴ አምላክ ሃሴት አደርጋለሁ” በማለት መናገሩ ተመሳሳይነታቸውን ይጠቁመኛል።
5. ቁ9 እግዚአብሄር በሃጥያት ምክንያት ቅጣት እንደደረሰበት የተረዳ ሰው፤ ሆኖም እግዚአብሄር እስራኤልን ሲቀጣ ሊያጠፋቸውና ሊገድላቸው ሳይሆን በስተ መጨረሻ ወደ ብርሃን ሊያመጣና ጽድቁን ማየት ወደሚችሉበት ለማምጣት እንደሆነ ሲያሳይ፤ ዕብ 12፡11-12ትም ደግሞ ይህንኑ ሃሳብ የተከተለና እግዚአብሄር ሲቀጣን ከቅድስናው እንድንካፈል እንጂ ለጥፋት እንዳልሆነ ያስተምረናል። ስለወደፊቱ እርግጠኛ ሆኖ የምናየው፤ አንደኛው እስራኤል ባለበት ሁኔታ ውስጥ እንደማይቀርና ከሁኔታው ውስጥ እግዚአብሄር እንደሚያወጣው እርግጠኛ መሆኑ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ አሁን እየተሳለቀበት ያለው ጠላቱ ሃፍረት እንደሚከናነብና ውድቀት እንደሚያገኘው ነው።
6. የእግዚአብሄር ሕዝብ ወደ ምርኮ እንደሚወሰድና የኢየሩሳሌም ቅጥሮችም እንደሚፈርሱ በተለያዩ ነብያት እንደተነገረ የምናውቅ ሲሆን፤ እግዚአብሄር በዚህ ክፍል ብቻ ሳይሆን በነብዩ በኤርሚያስም አንደበት የኢየሩሳሌም ቅጥር ተመልሶ የሚሰራበት ጊዜ እንደሚመጣ ሚክያስም በቁ11 ላይ ይናገራል፤ ከዚህም በተጨማሪ ድንበራቸው እንደሚሰፋ፤ አህዛብም ሁሉ ወደ እነርሱ እንደሚመጡም ጭምር ይናገራል። እስራኤል ከግብጽ እንደወጣበት ዘመን የእግዚአብሄርን ተአምራት ያያል፣ አህዛብም ተአምራቱን አይተው ያፍራሉ ሃይላቸውንም ያጣሉ፤ ከሚያዩት ተአምራት የተነሳ የተነሳ አህዛብ አፋቸውን በእጃቸው ይይዛሉ፣ ጆሯቸውም ትደነቁራለች፣ በፍርሃት ወደ እግዚአብሄር ይመለሳሉ፣ አስቀድመው የናቁትን እስራኤልንም ደግሞ ይፈራሉ።
7. በቁ19 እና በቁ19 ላይ ሰፋ አድርጎ እግዚአብሄር አምላካችን ለዘለዓለም እንደማይቆጣና ቅሬታዎቹ ለሆኑት ሕዝቦቹ ተመልሶ ይቅርታን የሚሰጥ እንደርሱ ያለ አምላክ እንደሌለ በመናገር የእግዚአብሄርን የመሃሪነት ባህርይ ነው አጉልቶ ሊያሳየን የሞከረው።
8. በቁ18-19 ውስጥ በእግዚአብሄር የመሃሪነት ባህርይ ላይ ያተኮረ እንደሆነ ስንመለከት፤ በዚህ በቁ20 ላይም ከዚያው ባህርይ ጋራ በተያያዘ፤ ነገር ግን ምህረት እንደሚያደርግ አስቀድሞ ከረጅም ዘመናት በፊት ቃል ኪዳንን ከእነ አብርሃምና ያዕቆብ የገባ በመሆኑና ያንን የገባውን ቃል እንደጠበቀ በማስታወስ ትኩረት ያደረገበት ባሕርይ የእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ጠባቂ አምላክ መሆኑ ነው።